የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት
ልሳነ ሕግ ጋዜጣ
**LISSANE HIG GAZETA**
Of the Benishangul Gumuz Regional State

21ኛ ዓመት ቁጥር 125
የካቲት 2007 ዓ/ም

**በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ**

21[th] Year Number 125
Assosa Fab 2015

ያንዱ ዋጋ ብር-----------
Unit price-----------

**<u>ማውጫ</u>**

<u>አዋጅ ቁጥር 125/ 2007 ዓ.ም</u>

**በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት የተሻሻለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ**

**<u>Content</u>**

**Proclamation No. 125/2015**

**The Re- Establitioment Proclamation of the Benishangul Gumuz Regional State Police Commission.**

<u>አዋጅ ቁጥር 125/ 2007</u>

**<u>የተሻሻለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ</u>**

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል እና የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ ሕግጋተ-መንግስታትንና ሕግጋተ -መንግስታቱን መሠረት አድርገው የሚወጡ ህጐችን የማስከበር ተልዕኮውን በብቃት በመወጣት የዲሞክራሲ ሥርዓትን ለመገንባት ፣ ሠላምን ለማስፈንና ልማትን ለማፋጠን በሚደረገው ሀገራዊ እንቅስቃሴ የበኩሉን ድርሻ ለማበርከት እንዲችል በተሻለ ሁኔታ እንዲደራጅ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ገለልተኛ የሆነና ሕብረተሰቡን በእኩልነት የሚያገለግል፤ በፖሊሳዊ ሥነ- ምግባሩ የታነፀና ብቃትና ጥራት ያለው አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል ተቋም መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ ፤

የፖሊስ አባላት መብታቸው የሚከበርበትን የተቀላጠፈ የፍትህ ሥርዓት ለማጠናከር እና የተጀመረውን የለውጥ አሠራርና የሰው ኃይል አስተዳደር ማሻሻያ ረገድ የተካሄዱትን ለውጦች በበቂ ሁኔታ የሚያካትት ህግ ማውጣት በማስፈለጉ፣

በክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን መልካም አስተዳደርና ሥነ -ምግባርን ለማስፈን ይቻል ዘንድ ቀደም ሲል የወጣው አዋጅ ያሉበትን ክፍተቶች ለማስወገድና ግልጽ ያልሆኑ አሰራሮችን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

**<u>Proclamation No. 125/2015</u>**

**<u>The Re- Establitioment Proclamation of the Benishangul Gumuz Regional State Police Commission.</u>**

WHERE AS, it has become necessary to reorganize the Regional police to enhance its capability its mission of ensuring the observance the constitutions of the Benishangul Gumz regional state and the Federal democratic Republic of Ethiopia and laws enacted in accordance with the constitutions, and there by play its part in the national efforts to build democratic system, maintain peace and enhance development;

WHERE AS, it has become necessary to ensure that the Regional police institution maintains its impartiality towards political parties , serve the public equally, maintain strict police discipline and deliver efficient and quality service;

WHERE AS, it has become necessary to enact a law which respect the rights of Regional police members , in order to strength the justice system and that includes the changes which has been made in the human resource management ;

WHERE AS, it has become necessary to

የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል ም/ቤት ተሻሽሎ በወጣው ክልሉን ህገ-መንግስት አንቀፅ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 ተተራ ቁጥር 1 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የሚከተለውን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልላዊ መንግስት ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር------ /2007 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓም የማያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ

1. "የፖሊስ አባል" ማለት መሠረታዊ የሆነ የፖሊስ ሙያ ስልጠና ተሰጥቶት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ተቀጥሮ የሚሰራ የተፈጥሮ ሰው ነው፤
2. "ቢሮ" ወይም "የቢሮ ኃላፊ" ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የቤኒሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልል የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዬች ቢሮ ወይም ቢሮ ኃላፊ ማለት ነው፤
3. "ኮሚሽን" ማለት የቤኒሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፖሊስ ኮሚሽን ማለት ነው፤
4. "ኮሚሽነር" ማለት የቤኒሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፖሊስ ኮሚሽነር ማለት ነው፤
5. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
6. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል፤

## ክፍል ሁለት
## የቤኒሻንጉል ጉምዝ ፖሊስ ኮሚሽን

### 3. መቋቋም

. የቤኒሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፖሊስ ኮሚሽን ከዚህ በኋላ " ኮሚሽን" እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው ተቋም የክልሉ መንግስት አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

. ኮሚሽኑ በህግና በሙያው የሚኖረው ነፃነት እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪነቱ ለቢሮው ይሆናል፡፡

### 4. ዋና መስሪያ ቤት

1. የኮሚሽኑ ዋና መስሪያ ቤት አሶሳ ከተማ ይሆናል፡፡
2. ኮሚሽኑ እንደ አስፈላጊነቱ በክልሉ ውስጥ በማናቸውም ሥፍራ በሥሩ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

### 5. ዓላማ

የኮሚሽኑ ዓላማ የፌደራሉንና የክልሉን ህገ-መንግስታት እና ሌሎች ህጎችን መሠረት አድርጎና በህብረተሰቡ ተሳትፎ ታግዞ ወንጀልን በመከላከል የክልሉን ህዝብ ሰላማዊ ኑሮ፣ ፀጥታ፣ የጋራ ደህንነት

avoid gabs in the previous proclamation in order to ensure good government and strict discipline in the Regional police Institution;

NOW THERE FORE. In accordance with the power vested in it under article49 (3) (3) (1) of the Revised constitution of Benishangul Gumuz Region, the following proclamation is enacted.

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as "THE BENISHANGUL GUMIZ REGINAL STATE POLICE RE-ESTABLISHIMENT PROCLAMATION NO. -----/ 2007.

### 2. Definition

Unless the context requires otherwise. In this proclamation:

1. "police officer " means a member of the Regional Police Commission
2. "Bureau" or bureau Head means the Administrative and Security Affaires Coordination Bureau of the Benshangul Gumuz Regional state or head of the bureau thereof respectively.
3. "Commission" means the Benishangul Gumuz Regional State Police Commssion.
4. "Commissioner" means Plice Commissioner Of Benishangul Gumuz Regional State.
5. Person means any natural or legal person.
6. Any expression in Masculine gender includes Feminine.

## PART TWO
## THE REGIONAL POLICE COMMISSION

### 3. Establishment

1. The Benishangul Gumuz Regional police Commissioner (here — in — after referred to as the "Commission ") is hereby established as a separate organ having its own legal personality in the Region.
2. Without prejudice to its legal and professional independence, the commission shall be accountable to the Bureau.

### 4.Head office of the Commission

1. The head office of the commission shall be in Assosa.
2. The Commission may stablish branch offices in other areas of the region as may be necessary.

### 5.Objective

The Commission shall have the objective to maintain and ensure peace and security of the public and the state by respecting and ensuringthe observance of the constitution of the Regional and federal Government and prevent crime through the participation of the

በማስጠበቅ ህግና ሥርዓትን ማስከበር ነው፡፡

6. <u>የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር</u>

ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በህገ መንግስታዊ ሥርዓቱ፣በመንግስትና በክልሉ ፀጥታ እና በሰባዊ መብቶች ላይ የሚፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶችንና የወንጀል ስጋቶችን እንዳይፈጸሙ ይከላከላል፡፡
2. በክልሉ ፍርድ ቤቶች የሥልጣን ክልል ሥር የሚወድቁ ወንጀሎችን ይመረምራል፣ ተጠርጣሪዎችን በህጉ መሰረት ይይዛል፣በቁጥጥር ሥር ያውላል
3. ለክልሉ ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት ሁኔታው በሚጠይቀው መጠን አስፈላጊውን ጥበቃ ያደርጋል
4. በክልሉ መንግስት ጥቅሞችና ተቋሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ይከላከላል፣ይመረምራል
5. የክልሉን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመመርመር የሚረዳ መሆኑ በሚገባ የታመነበትን ማስረጃ ወይም መረጃ ከማንኛውም ተቋም በመሰብሰብ ይመረምራል፡፡
6. በተለያዩ ክልሎች ወንጀል ፈጽመው ወደ ክልላችን የሚገቡ ተጠርጣሪዎችን እና በህገ ወጥ መንገድ ሠርገው የሚገቡ የውጭ ሃገር ዜጐችን ይከላከላል፣ ይከታተላል ሲገኙም ይዞ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፣
7. ህብረተሰብን በማሳተፍ ወንጀልንና የትራፊክ አደጋዎችን ለመከላከል፣ ለመመርመር የሚያስችሉ እስትራቴጅዎችን ይቀርጻል፣ የወንጀል ሪከርዶችን ይይዛል፣ ይተነትናል ስታቲስቲክስና መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ውጤቱንም በመገምገም ተግባራዊ ያደርጋል፣
8. በማስረጃነት ወይም በኢግዚቢትነት የሚያዙ ንብረቶችን በአግባቡ ጠብቆ ይይዛል፣ እንደአስፈላጊነቱም በህግ አግባብ ለሚመለከታቸው ይመልሳል፣
9. የወንጀል ሥራ ፍሬዎች ወይም ውጤቶች የሆኑ ንብረቶች እንዲከበሩለት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ጥያቄ ያቀርባል፣
10. በህግ የዳኝነት ሥልጣን በተሰጣቸው ፍርድ ቤቶች የሚሰጡትን ትዕዛዞች ወይም የሚተላለፉለትን ውሳኔዎች ያከብራል ይፈፅማል፣
11. የወንጀል ምርመራን በተመለከተ በየደረጃው በሚገኙ የፌደራልና የክልሉ አቃቤያነ ህግ እና ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በጋራ ይሰራል፣
12. በክልሉ የሰላማዊ ሰዎችንና በወንጀል የተጠረጠሩ ግለሰቦችን የአሻራ ሪኮርዶች በማዕከል ይይዛል፣የሰነድና የጣት አሻራ ማስረጃ ለሚጠይቁ ግለሰቦች ወይም ድረጅቶች ተመጣጣኝ ዋጋ በማስከፈል አገልግሎት ይሰጣል፣ ከወንጀል ነጻ ማስረጃ ይሰጣል፣
13. ከፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን በሚሰጠው ውክልና መሰረት የፌደራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮችን ይከላከላል፣ይመረምራል፣
14. በክልሉ ውስጥ የጥበቃ ስራ የሚያከናውኑ የግል ተቋማት ስራዎቻቸውን በአግባቡ ማከናወናቸውን ይከታተላል፣ በየወቅቱ ስልጠና ይሰጣል፣ የሙያ ስራ ፍቃድ ይሰጣል ፣
15. ከፌደራል ፖሊስ በሚሰጥ ውክልና መሰረት የጦር መሳሪያ ይመዘግባል፣ፍቃድ ይሰጣል ፣በግለሰቦችና በድርጅቶች ሊያዙ የሚገባቸውንና የማይገባቸውን የጦር መሳሪያዎችን ይለያል፣

community and there by maintain peace. Security and common welfare of the people of the Region and ensure the observance of law and order.

6. <u>Powers and Function of the Commission</u>

The Commission shall have powers and functions to:

1. Prevent any treat and acts of crime against the constitution and the constitutional order, security of the government and the state and human rights;
2. Investigate crimes that fall under the jurisdiction of the courts of the Region and arrest and detain suspects.
3. Give the required necessary security protection to higher officials of the Region
4. Prevent and Investigate crime against the interest and Institution of the Region;
5. Collect any evidence or information from any institution which helps to prevent and investigate crime indangours Regional security;
6. Prevent, follow up, and transfer to the concerned organ suspects, if found, who committed crime in deferent regions and entered in to the region, or foreigners who illegally entered in to the region;
7. With the participation of the public design strategies to prevent, investigate crimes and traffic accesidents, maintain and execute the result of evaluation;
8. Properly maintain properties which serve as evidence and exhibit; as may be necessary return it to concerned body in accordance with law;
9. Apply to courts vested with judicial power to detain properties which are fruits or results of crime;
10. Respect and execute orders made and decisions passed by organs with judicial power;
11. Work in collaboration with of Federal and Regional Prosecutors found at any level and other concerned bodies in respect to Crimiminal investigation;
12. Centrally organize and keep innocent and suspected individual print records, provide documents and figure print evidences to individuals or organizations with commensurate payment and issue certificates to individuals with no criminal record;
13. With the delegation of federal Police commission, Prevent and investigate crimes falls under the jurisdiction of federal courts;
14. Follow proper performance of private institutions which engage in security service , provide timely training and issue

ይቆጣጠራል፣ ለልማት ስራ የሚውሉ ተቀጣጣይ ፈንጅዎችን፣

16. በክልሉ ውስጥ በተለያዩ የአስተዳደር ዕርከኖች በተዋረድ ዞን ፖሊስ መምሪያዎች፣ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤቶች፣ ፖሊስ ጣቢያዎች፣የኮሚንቲ ፖሊሲንግ እና ሌሎች አደረጃጀቶችን ያቋቁማል፣ ያደራጃል ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

17. የተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ አደጋ ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ከበጎ አድራጎት ማኅበራት እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አከላት ጋር በመተባበር ሰላምና ደህንነትን ይጠብቃል፣

18. የሽብርተኝነት ድርጊት ሊፈጸም እንደሚችል በቂና ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሊኖርና ድርጊቱንም ቀድሞ ለመከላከል ድንገተኛ ፍተሻ ማድረግ አስፈላጊነቱ ሲታመንበት በማነኛውም ጊዜ በተጠረጠሩ አካባቢ ያሉ ተሽከርካሪዎች ፣ ተሳፋሪዎችንና እግረኞችን በማስቆም ድንገተኛ ፍተሸ የማድረግ ስራ ያከናውናል፣

19. ኮሚሽኑ በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል የፖሊስ ሞያ ብቃትና አገልግሎት ለማሻሻል የሚረዱ የሪፎርም ሥራዎችን ከተቋሙ ልዩ የሥራ ባህሪ አንፃር ያደራጃል፣ጥናቶችን ያተናል፣ያስተናል ፣በስራ ላይ እንዲውሉም ያደርጋል፣

20. ለክልሉ ፖሊስ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል መልምሎ ያሰለጥናል፣ በአስፈላጊው ቦታ ይመደባል፣

21. የመንገድ ላይ ትራፊክ እንቅስቃሴና ፍሰትን ይቆጣጠራል፣በማንኛውም ሁኔታ የተዘጉ ምንገዶችን ያስከፍታል ፣የትራፊክ ደህንነት ትምህርት ይሰጣል፣ የትራፊክ አደጋዎችን ይመረምራል፣በደንብ ተላላፊዎች ላይም እርምጃ ይወስዳል፣

22. በፖሊስ ምልመላ እና ቀጠራ፣ በስንብት በትምህርትና ስልጠና፣ በማዕረግ እድገት አሰጣጥ፣ በደንብ ልብስ አለባበስ፣ በትጥቅ እና በሌሎች ጉዳዬች ስታንዳርዶችን ያወጣል፣

23. በአስረጅነት አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ የወ/ምርመራ መዛግብቶችን፣ ሠነዶችን፣ አሻራዎችንና ተያያዥነት ያላቸውን ሪከርዶች ከሚመለከታቸው አካለት ጋር በመቀናጀት እንዲወገዱ ያደርጋል፡፡ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል፣

24. የአባላትን ልዩ ልዩ አበሎችን እና ጥቅማ ጥቅሞችን አጥንቶ ለቢሮው ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

25. አባላት እንደ ሥራ ባህሪያቸው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉበትን ቢሮዎችና የመኖሪያ ካምፖች ይሰራል፣

26. ለሥራ የሚያስፈልጉ ድጋፍ ሰጭ ሲቪል ሠራተኞችን በመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣

27. በክልሉ ውስጥ ፖሊስ ትምህርትና ስልጠና ማዕከላትን ያቋቁማል ፣ይመራል ይቆጣጠራል፣

28. የፎረሲክ ምርመራዎችን ያደርጋል፣ስለመረመረው ጉዳይ ማስረጃ ይሰጣል፣ለፍርድ ቤት ወይም ለጠያቂ አካል የሞያ ምስክርነት ይሰጣል

29. በፎረንሲክ ምርመራ ጉዳዮች ላይ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡

proffecinal license certificate;

15. With the delegation of federal Police commission register weapons, issue license and determine weapons to be carried by individuals and institutions;

16. Establish, organize, coordinate and control police offices and stations at different administrative levels of the region.

17. Maintain peace and security in the case of emergency situations due to the occurrence of natural or manmade disasters, and work in collaboration with concerned government organs, charities and associations in providing assistance to victims.

18. Where there is sufficient ground to suspect the likely commission of terrorist act and where it is believed that surprise search necessary to prevent Such act, stop and search vehicles and pedestrians found in suspected areas, arrest suspects and seize materials and carry out investigation.

19. Conduct and implement studies that may be contribute for the proper accomplishment of its mission and for the improving the professional competence and service of the police.

20. Recruit and train the manpower necessary for the police in the Region and give placement at necessary place.

21. Control traffic movements and flows on roads, make to open road closed by any conditions, give traffic security educations, investigate traffic accidents and take a proper measure on those who breaches traffic rules.

22. Issue standards on police recruitment, employment, dismissal, education and training, ranks, wearing of uniform, equipment and other related matters.

23. Dispose, in collaboration with concerned organs investigation files, finger prints and Other related documents that have lost their evidentiary values.

24. Study and submit to the government salary scales and allowances applicable to police officers and implement same upon approval

25. Cause the construction of offices and resident camps to be used by its units and police officers;

26. Recruit administer and dismiss supportive staff in accordance with the regional civil service laws.

27. Establish police training centers facilitate domestic and foreign continuing education and training for police officers;

28. Conduct forensic investigation and submit its findings and provide expert witness to court or the requesting organ;

29. Work in collaboration with federal police

30. የንብርት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋል፣ በራሱ ስም ክስ ይመሰርታል ይከሰሳል፣
31. በሌሎች ህጎች ድንጋጌዎች ለክልሉ ፖሊስ የተሰጡ ስልጣንና ተግባራትን ያከውናል፣
32. ሌሎች በክልል መስተዳድሩና በቢሮው ህግን መሰረት አድርገው የሚሰጡ ተጨማሪ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 7. የኮሚሽኑ አቋም

ኮሚሽኑ፡-

1.በክልሉ ርዕሰ መስተዳደር የሚሾሙ አንድ ኮሚሽነር እና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ኮሚሽነሮች፣
2.የኮሚሽኑ ማኔጅመንት አባላትና ረዳት ኮሚሽነሮች፣
3.በዞንና በወረዳ ደረጃ የሚቋቋሙ ማኔጅመንት አባላት፣
4.ሌሎች የፖሊስ የጸረ-ሽምቅ አባላትና ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ሲቪል ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

## 8. የኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባር

1. ተጠሪነቱ ለቢሮው ሆኖ የኮሚሽኑን ስራ በበላይነት ይመራል ፣ያስተባብራል፡፡
2.የኮሚሽኑን ምክትል ኮሚሽነሮች፣ የፖሊስ ኮሌጁን ዳይሬክተርና ምክትል ዳይሬክተር ዕጩ ለርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት በማቅረብ ሹመታቸውን ያስፀድቃል፣
3.የኮሚሽኑን ረዳት ኮሚሽነር ሹመት ያጸድቃል፣
4.የክልል የስራ ሂደት ባለቤቶችን፡ የጸረ-ሽምቅ አመራሮችን፡ ኮሌጅ የስራ ሂደት ባለቤቶችን፣ዞን ፖሊስ መምሪያ ሃላፊዎችን፣ዞን የስራ ሂደት ባለቤቶችን፣የወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት ሃላፊዎችንምደባ ያጸድቃል፡፡
5.ይህን አዋጅና አዋጁን ተከትሎ የሚወጡ ድንብ እና መመሪያዎችን በበላይነት ያስፈፅማል፣
6.በስሩ የሚያገለግሉ ድጋፍ ሰጭ ስቪል ሰራተኞችን በክልሉ ስቪል ሰርቪስ አዋጅና ደንብ መሰረት ይቀጥራል፣ያስተዳድራል፣ያሰናብታል፡፡
7. የኮሚሽኑን ዓመታዊ እቅድና ረቂቅ በጀት ያቀርባል፣ሲፈቀድምበስራ ላይ ያውላል፣በተፈቀደው በጀት መሰረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል ፣የስራ እንቅስቃሴና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ያቀርባል፣
8. በዲስፕሊን ተሰናብተው በኮሚሽኑ የሰው ሃይል አስተዳደር በኩል በሚቀርቡ የይግባኝ አቤቱታዎች የሰው ሃይል አስተዳደሩ በሚሰጠው የውሳኔ ሃሳብ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፣በአቤቱታናቅሬታ ሰሚ በኩል የሚቀርቡና ተጣርተው የሚቀርቡ ማናቸውም የዲስፕሊን ውሳኔ ሃሳቦች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፣
9. ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኮሚሽኑን ይወክላል፣
10. ለሥራው ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል በየደረጀው ለሚገኙ ኃላፊዎች ውክልና ይሰጣል፣
11. ከፌደራል ፖሊስ ጋር የስራ ግንኙነት በመፍጠር የመረጃ

commissions on matters relating to forensic investigation;

30. Enter into contracts own property, Sue and be sued in its own name.
31. Exercise the powers and duties given to the regional police by the provisions of other laws.
32. Exersice additional dutes given, in accordance with laws, by the administrative council and the bueraro.

## 7. Organization of the Commission

The commission shall have the following organs.

1. Commissioner and Deputy Commissioner appointed by the president up on recommendation of the Bureau,
2. Management committees and Assistance commissioners,
3. Management committees established under Zone and Woreda levels,
4. Other police officers and supporting staff necessary for its activities.

## 8. Power and Duties of the Commissioner

1. The Commissioner shall direct, administer and control the activities of the Commission,
2. Submit to the President, for approval, the appointment of deputy Commissioners, Directors and Deputy Director of police college,
3. The Commissioner shall approve the appointment of assistances commissioners,
4. Approve the appointment of process owners under the commission,
5. Effect the implementation of the regulation and directives issued accordance to the proclamation,
6. Recruit, adminster and dismiss other employes of the commission in accordance with the regional cevil service proclamation,
7. Submit to to the bureau the annoal work plan buget of the Commission, implement same upon approval, effect payment in accordance to the approved budget and submit operational and financial report to the regional Finance and Economy,
8. Render a final decision on administrative compliant of police officers dismiss due to discipline masseurs,
9. Represent the commission in all its dealings with third parties,
10. The commissioner may delegate part of

ልውውጥ ያደርጋል ፤የአቅም ግንባታ ስራዎችና እንዲከናወኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣.

12. በክልል መስተዳድርና በቢሮው ህግን መሰረት አድርገው የሚሰጡትን ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል፡፡

9. **<u>የምክትል ኮሚሽሮች ሥልጣንና ተግባር</u>**

ምክትል ኮሚሽነሩ ተጠሪነቱ ለኮሚሽነሩ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. ስትራቴጅክ በሆነ መንገድ በማቀድ፣በማደራጀት፣በመምራትና በማስተባበር ኮሚሽነሩን ይረዳሉ፤ይገመግማል አፈፃፀሙንም ሪፖርት ያቀርባል፣
2. ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ እርሱን ተክቶ ይሰራል፣ሆኖም ምክትል ኮሚሽነሮቹ ከአንድ በላይ ከሆኑ በሹመት አሰጣጥ ሂደት ቅድሚያ ሹመት የተሰጠው ይወከላል፡፡
3. በኮሚሽነሩ ተለይተው የሚሰጣቸውን ተግባራት ያከናውናሉ፡፡

10. **<u>የማኔጅመንት ኮሚቴ አባላት</u>**

1. የማኔጅመንት ኮሚቴው አባላት፡-

ሀ.የክልሉ ፖሊኮሚሽነር..............................ሰብሳቢ

ለ.ምክትኮሚሽነሮች....................................አባላት

ሐ.ረዳት ኮሚሽነሮችና የስራ ሂደት ባለቤቶች ................አባላት

መ.እንደ አስፈላጊነቱ የማኔጅመንት ኮሚቴው በሚወስነው መሠረት የሚመደቡ ሌሎቹ የኮሚሽኑ ሃላፊዎች.............አባላት

ሠ. የኮሚሽነሩ ጽ/ቤት ሃላፊ የማኔጅመንት ኮሚቴው ፀሐፊ ሆኖ ይመደባል፡፡

11. **<u>የማኔጅመንት ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር</u>**

የማኔጅመንት ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለኮሚሽነሩ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የኮሚሽኑን አደረጃጀት፣ አወቃቀር እና አሠራር በሚመለከቱ ጥናቶች ላይ ሊወሰዱ የሚገባቸውን ዕርምጃዎች በመገምገም ያጸድቃል፡፡
2. የኮሚሽኑን የበጀት ረቂቅ በመገምገም አቅርቦ ያስፀድቃል፣
3. የኮሚሽኑን እስትራቴጅክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድና የሥራ አፈፃፀም ይገመግማል፣
4. የኮሚሽንኑን አዋጅና ደንብ በየጊዜው በመገምገም እንዲሻሻል ያስደርጋል፤ ረቂቅ ማሻሻያዎችንም ገምግሞ ያስጸድቃል
5. የኮሚሽኑን ልዩ ልዩ የስራ መመሪያዎችን ያስጸድቃል፤ በስራ ላይ እንዲውሉ መደረጋቸውን ይከታተላል፣
6. የኮሚሽኑን የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ዕቅዶችን በፍላጎት ግምገማ ጥናት ላይ ተመስርቶ ያጸድቃል፣
7. ሌሎች የኮሚሽኑን አሰራሮችን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ውሳኔዎችን ያሳልፋል፡፡

12. **<u>በጀት</u>**

ኮሚሽኑ ከክልሉ መንግስት በሚመደብለት በጀት ይተዳደራል፡፡

his powers and duties to subscuent officials the commission to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the commission,

11. By establishing relation with Federal police Commission exchange information and carry capacity building activities,
12. Exercise other activates given by the president and bureau, in accordance with law.

9. <u>Power and function of the Deputy Commissioner</u>

The Deputy Commissioner shall be accountable to the and under take the following activities:

1. Strategically assist the Commissioner in planning, Organising, directing and coordinating the activities of the commission,
2. Act on behalf of the commissioner in his absence or when he is unable to discharge his duties,
3. The deputy commissioner shall discharge specified duties entrusted to him by the commissioner.

10. <u>Management Committee</u>

1. The management committee of the commission shall have the following members;

a) The Commissioner ------------------------------------------------------- chair person

b) Deputy Commissioners ------------------------------------------------ members

c) Assistance Commissioners and head of process owners --------------- members

d) Other officials of the Commission to be designated by the commissioner as may be necessary ---------------------------------------------------------------------------- members

e) Office head of the Commission shall be appointed as secretary of the management.

11. <u>Powers and Duties of the Management Committee</u>

The management Committee shall have the following powers and duties:

1. Review studies of the organizational structure of the commission, budget proposals and performance reports to be submitted to the government,
2. Evaluate the implementation of laws governing the operation of the Commission forward amendment proposals where necessary,
3. Approve operational directives of the Commission and ensure their implementation,
4. Approve police officer higher education and training plans on the basis of need assessment studies,
5. Deliberate on other issues that may be referred to it by the Commissioner.

12. <u>Budget</u>

The budget of the Commission shall be allocated

13. **የሂሳብ መዛግብት**

1. ኮሚሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል፣
2. የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በውስጥ ኦዲተር እና በክልሉ ዋና ኦዲተር ወይም ዋና ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

## ክፍል ሦስት
## የሰው ኃይል ልማትና አስተዳደር

14. **የሰው ሀይል እቅድ**

ኮሚሽኑ የስትራቴጅክ እቅዱን መሰረት በማድረግ አጭር ፣የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የሰው ሃይል እቅዶችን አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

15. **የሰው ሀይል አስተዳደር**

1. ኮሚሽኑ የፖሊስ አባላትን በክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት በሚወጣው ደንብና ደንቡን ተከትለው በሚወጡ መመሪያዎች መሰረት ይመለምላል፣ ያሰለጥናል፣ ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፡፡
2. ኮሚሽኑ አሰፈላጊ ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞችን በክልሉ ሰቪል ሰርቪስ ህጎች መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፡፡

16. **የግዴታ አገልግሎት ዘመን**

1. የማንኛውም የክልሉ ፖሊስ አባል የግዴታ አገልግሎት ዘመን ሰባት ዓመት ይሆናል፡፡ዝርዝር አፈፃፀሙም በደንብ ይወሰናል፣
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ስር የሰፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የማንኛውም የክልሉ ፖሊስ አባል ቅጥር ከሚከተሉት ምክንያቶች
   ሀ- በሞት ሲለይ
   ለ- በደንቡ መሠረት በገዛ ፈቃዱ የስንብት ጥያቄ አቅርቦ ጥያቄው ተቀባይነት ሲያገኝ
   ሐ- በሕመም ወይም በአካል ጉዳት ምክንያት ለሥራው ብቁ አለመሆኑ በህክምና ቦርድ ሲረጋገጥ፣
   መ- በሥራ አፈፃፀም ወይም በዲስፕሊን ጥፋት ሲወሰንበት ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ይሆናል፣
   ሠ- በፍርድ ቤት በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘና ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ መሰረት ወንጀሉ ለስራ ብቁ አያደርገውም ተብሎ ሲወሰን፣
   ረ- በዕድሜ ምክንያት በጡረታ ሲገለል

17. **የፖሊስ አባላት መብቶች**

1. *ማንኛውም የክልሉ ፖሊስ አባል፡-*
   *ሀ.* በክልሉ መንግስት በሚፀድቅ የደመወዝ ስኬል መሠረት ደመወዝ ያገኛል፣
   *ለ.* የጡረታ መብት ይኖረዋል፣
   ሐ- ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው መሰረት ልዩ ልዩ አበሎች የደንብ ልብስና ህክምና አግልግሎት ያገኛል፡፡
   መ- የጡረታ መውጫ ዕድሜ ከመድረሱ በፊት አምስት ዓመት ሲቀረው ጀምሮ የጡረታ መብት እንዲከበርለት

by Government of the Region.

13. Books of Account

1. The Commission shall keep complete and accurate books of account,
2. The books of account and documents related to finance shall be audited by the Auditor General of the Region or by auditor designated by the auditor General.

## PART THREE
## Regional Police Administration

14. Human Resource Plan

The Commission shall develop and implement short, medium and long term human resource plans based on its strategic plan.

15. Human resource administration

1. The Commission shall recruit, train, employ, administer and dismiss police officers in accordance with a regulation issued by the regional administrative council,
2. The Commission shall recruit, train, employ, administer and dismiss the necessary supportive stuff in accordance with the regional civil service law.

16. Mandatory term of Service

1. The mandatory term of service of any police officers of the region shall be seven years. Particulars as to it implementation shall be determined by a regulation issued based on this proclamation,
2. Without prejudice to sub article 1 of this article, the employment contact any police officer may be terminated by one or any of the following reasons;
   a. Upon death,
   b. Where a request for release is made by the police officer and is admired in accordance with the relevant regulation,
   c. When a medical board confirmed unfitness for the job on account of illness,
   d. Subject to particulars to determined by regulation, where the officer is charged and found guilty by regular court,
   e. Owing to gross inefficiency or breach of discipline,
   f. Upon retirement.

17. Rights

1. Any police officer of the region shall
   a) Get a salary in accordance with the salary scale,
   b) Be entitled to ration, various allowance, uniform and medical services, in accordance to the administrative regulation of the Commission,
   c) Five year prior to retirement age be entitled to pension in accordance with

አባሉ ሲጠይቅ እና መስሪያ ቤቱ ሲፈቅድ የጡረታ መብት ይከበርለታል ሆኖም የአገልግሎት ዘመኑ ከሃያ አምስት ዓመት ያላነሰ መሆን አለበት፣

ሠ. ከፖሊስ ተግባሩ ጋር በተገናኘ ሁኔታ ሥራውን በማከናወን ላይ እያለለሚደርስበት የወንጀልም ሆነ የፍታብሔር ተጠያቂነት ዝርዝር አፈጻጸሙ አዋጁን ተከትሎ በሚወጣው ደንብ መሰረት የሚወሰን ሆኖ በመ/ቤቱ ባለሙያ የጥብቅና አገልግሎት ያገኛል፤

ረ. በማንኛውም አጋጣሚ የበላይ ኃላፊዎችን በአግባቡ የመጠየቅ፣ ስህተቶችን ሲያይ የመጠቆምና በመ/ቤቱ ውስጥ በውይይት ችግሮችን የመፍታት መብት አለው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የሥልጣን ተዋረዱን ጠብቆ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

ሰ. ማንኛውም የክልሉ ፖሊስ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣው ደንብ በሚወሰነው መሰረት የዓመት እረፍት ፈቃድና ሌሎች ልዩ ልዩ ፈቃዶች ይሰጠዋል

3. በኮሚሽኑ የሥራ ባህሪይ ምክንያት በጋራ መኖርን ለሚጠይቁ ሥራዎች አባላት የተሟሉ የመኖሪያ ካምፖች ያገኛሉ፣
4. በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ ውስጥ ከተጠቀሱት ውጭ ያሉ መብቶችን በተመለከተ የፌደራሉና የክልሉ ሲቪል ሠርቪስ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በፖሊስ አባላት ዘንድም ተፈፃሚዎች ይሆናሉ፡፡

18. <u>የፖሊስ አባላት ግዴታዎች.</u>

*ማንኛውም የክልሉ የፖሊስ አባል፡-*

1. ህገ- መንግስቱንና ህገ- መንግስታዊ ሥርዓቱን ከማንኛውም አደጋ መጠበቅ አለበት፣
2. በህገ- መንግስቱ የተረጋገጡትን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሳይሸራርፉ
3. የወንጀል ህግና የህጉ ማስፈፀሚያ የሆነውን የሥነ- ሥርዓት ህግ መሠረት በማድረግ ሥራውን ማከናወን አለበት፣
4. የሀገሪቷንና በሥራው አጋጣሚ ያወቃቸውን የተቋሙን የሥራ ሚስጥሮች መጠበቅ አለበት፣
5. ፖሊሳዊ ሥራውን ሲያከናውን ማንነቱን የሚገልፅ መታወቂያ የማሳየት ግዴታ አለበት፣
6. ከየትኛውም የፖለቲካ ድርጅት አባልነት ነጻ መሆን ይጠበቅበታል፡፡
7. ማንኛውም የክልሉ ፖሊስ አባል ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣው ደንብና መመሪያ መሠረት ተዛዋውሮ የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

19. <u>የዲሲፕሊን ዕርምጃዎች አወሳሰድ</u>

ማንኛውም የክልሉ ፖሊስ አባል የሥነ- ምግባር ደንቦችን የጣሰ እንደሆነ ጥፋቱ በኮሚሽኑ የዲሲፕሊን ደንብና መመሪያ መሰረት ይታያል፡፡

20. <u>ስለ ፖሊስ ማዕረጎች</u>

1. የኮሚሽኑ የፖሊስ አባላት ደረጃቸውንና ሀላፊነታቸውን የሚገልጽ ማዕረጎችና ምልክቶች ይኖራቸዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከቱት ማዕረጎች ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናሉ፡-

ሀ/ ኮንስታብል

pension law,

d) Be provided with attorney by the Commission for liability incurs while properly discharge his job. Particulars shall be determined by a regulation,

e) Entitled to pension right in accordance with pension law,

f) Have the right to appropriately question superiors under any circumstances, indicate mistakes he observes, and resolve problems through negotiation, he may lodge appeal as may be necessary by complying with the chain of commands,

g) Entitled to obtain annual leave and various leaves. The detail shall be determined by directives.

2. Entitled to get comp due to the work character of the Commission which require group work. With respect to the rights not incorporated in this proclamation and in regulation issued to implement it, the federal and the regional civil service laws, regulations and directives shall apply to police officers.

18. <u>Duties of police officer</u>

Any police officer of the Commission shall

1. Protect the constitution and the constitutional orders from any danger,
2. Respect and enforce human and democratic rights guaranteed under the constitution
3. Exercise its reasonability in accordance with criminal and procedure laws.
4. Keep secrets of the nation and of secrets of the institutions obtained by reason of his profession
5. Have the duty to show identity card while performing his job,
6. Free from any political party,
7. Any police officer shall work in rotation, in accordance with the law issued subsequent to this proclamation.

19. <u>Displinary measure</u>

Any breach of discipline shall be entertained according to the disciplinary regulations and directive of the commission.

20. <u>Police Ranks</u>

1. Police officers of the commission shall

ለ ረዳት ሣጅን
ሐ/ ምክትል ሣጅን
መ/ሣጅን
ሠ/ ዋና ሣጅን
ረ/ ረዳት ኢንስፔክተር
ሰ/ ምክትል ኢንስፔክተር
ሸ/ ኢንስፔክተር
ቀ/ ዋና ኢንስፔክተር
በ/ ምክትል ኮማንደር
ተ/ ኮማንደር
ቸ/ ረዳት ኮሚሽነር
ኀ/ ምክትል ኮሚሽነር
ነ/ ኮሚሽነር

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተመለከቱት የፖሊስ አባላት ማዕረጎች የየራሳቸው ምልክት ይኖራቸዋል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

21. <u>ሜዳይ፣ ሪቫንና የምስክር ወረቀት</u>

የፖሊስ ኮሚሽን ተልዕኮ ግቡን እንዲመታ ከፍተኛና የላቀ ፖሊሳዊ ተግባር ለፈፀመ፣አዲስ ግኝት ላስገኘ ወይም ለፈጠረ አባል ወይም የቡድን አባላት እና ረጅም አገልግሎት ላበረከተ አባል ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው መሰረት ሜዳይ፣ ሪቫንና የምስክር ወረቀት ተሸላሚ ይሆናል፡፡

22. <u>የጡረታ መውጫ ዕድሜ</u>

1. ማንኛውም የክልሉ ፖሊስ አባል በጡረታ የሚገለልበት ዕድሜ ጣሪያ፡-
ሀ. ከኮንስታብል እስከ ዋና ሣጅን ማዕረግ ያለው 50 ዓመት.
ለ. ከረዳት ኢንስፔክተር እስከ ኢንስፔክተር ማዕረግ ያለው 52 ዓመት.
ሐ. ዋና ኢንስፔክተር እና ከዚያ በላይ ማዕረግ ያለው 55 ዓመት.
2. ከዚህ በላይ ከንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተደነገገው ቢኖርም አባሉ በልዩ ሙያው በአጭር ጊዜ ሊተካ የማይችል እና ለመስሪያ ቤቱ ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለአንድ ጊዜ ብቻ ከ5 /አምስት/ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ አገልግሎቱ ሊራዘም ይችላል፡፡ ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

23. <u>የተከለከሉ ድርጊቶች</u>

ማንኛውም የፖሊስ አባል ተግባሩን በሚያከናውንበት ጊዜ፡-
1. ኢሰባዊ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝና ድርጊት መፈጸም ወይም
2. በዘር፣ በብሔር፣ በብሄረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት ፣በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ማድረግ በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡

24. <u>ስለ አገልግሎት አሰጣጥ እና ቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት በኮሚሽኑ ውስጥ የክልል ፖሊስ አቤቱታ ሰሚ አካል ተቋቁሟል፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የተቋቋመው

have ranks and insights which express their position and responsibility.

2. Ranks expressed in sub article one of these articles are
A. Constable
B. Assistant sergeant
C. Deputy sergeant
D. Sergeant
E. chief sergeant
F. assistant inspector
G. deputy inspector
H. inspector
I. chief inspector
J. deputy commander
K. Commander
L. assistant commissioner
M. deputy commissioner
N. Commissioner.

3. Ranks of police officers specified under sub article 2 of this article shall have their respective insignia.

21. <u>Medals, Ribbons and certificates</u>

A police officer or a group of police officers play a great role for the achievement of the goal of the institution, Create a new invasion, and serves for long period shall be entitled to medals, ribbons and certificates. The details shall be determined by regulation.

22. <u>Retirement age</u>

1. The retirement age applicable to police officers shall be as follows
a) For police officers having ranks from constable to chief sergeant 50 Years,
b) For police offers having ranks from assistance inspector to inspector 52,
c) For police officers from chief inspector and above 55 years.
2. Where it is in the interest of the Commission, any police officer may be retained in service beyond the age of retirement for a period not exceeding five years. The particulars shall be determined by a regulation.

23. <u>Prohabitions</u>

In exercising police functions, it is prohibited to:
1. Commit any inhuman or degrading treatment or act;
2. Make discrimination based on race, nationality, color, gender, language, religion, political outlook social back ground, wealth, birth and any other

ቅሬታ ሰሚ አካል ተጠሪነቱ ለኮሚሽኑ ሆኖ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፣

ሀ. የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን አካላት የስራ አፈጻጸም ወይም አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከግለሰብ፣ ከመ/ቤት/ ከድርጅት ወይም ከህዝብ አቤቶታዎችን፣ አስተያቶችን ወይም ትችቶችን ይቀበላል፣ ያጣራል፣

ለ. በሚቀርብለት አቤቱታ መነሻነት ማናቸውንም የክልሉ ፖሊስ አባል ስለአቤቱታው ይጠይቃል፣ መልስ እንዲሰጥ ያደርጋል፣በማጣራት መወሰድ የሚገባውን እርምጃ ያለውን አስተያት ለኮሚሽኑ ያቀርባል፣

ሐ. የቀረበለትን አቤቶታ ፣ አስተያየት ወይም ትችት በማጣራት መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ያለውን አስተያየት ለኮሚሽኑ ያቀርባል፣

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 /ለ/ መሠረት መልስ እንዲሰጥ የታዘዘ የክልሉ ፖሊስ አካል /አባል/ በ20 ቀናት ጊዜ ውስጥ መልስ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

25. ኮሚሽኑ ከኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ጋር ስለሚኖረው ግንኙት

1. የፌደራል ጉዳዩችን በሚመለከት ከፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ጋር የሥራ ግንኙነት ይኖረዋል፣
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1)ድንጋጌ መሠረት በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ተወክሎ የፌደራል ወንጀል ጉዳዬችን ሲከላከል፣ሲመረመርና ሲያጣራ ሌሎችንም ጉደዬች ውክልና ተሰጥቶት ሲያከናውን ለዚሁ ኮሚሽን ተጨማሪ ተጠሪነት ይኖረዋል፣
3. ኮሚሽኑ ከፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ጋር እንዳስፈላጊነቱ፣ የስልጠና፣ የትምህርት፣ የሙያና፣ የቴክኒክ ምክር፣ አገልግሎቶች ድጋፍ ግንኙነት /ትብብር/ ይኖረዋል፡፡
4. ኮሚሽኑ ወንጀልን፣የመንገድ ትራፊክ ደህንነትንና ፀጥታን በሚመለከቱ ጉዳዩች ላይ ለጥናት፣ለሪፖርትና ስታትስቲክስ አላማ ለፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ያስተላልፋል፣
5. ለፖሊስ ምልመላና ቅጥር፣በትምህርትና ስልጠና በማዕረግ ዕድገት አሰጣጥ፣ በደመወዝና ልዩ ልዩ አበሎች አከፋፈል፣ በትጥቅ፣ በደንብ ልብስ አለባበስ፣ በስንብት፣ በጡረታ ዕድሜና በመሳሰሉት ጉዳዬች ወጥነት /እስታንድ/ እንዲኖር ከፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ጋር በጋራ ይወስናል፡፡

26. የአሰራር መርሆች

1. በኮሚሽኑ መዋቅር በየደረጃው ባሉት ኃላፊዎችና ሠራተኞች የቡድን አሰራር ዋና የተግባር አፈጻጸም አቅጣጫ ይሆናል፣ የቡድን አሰራሮች የጋራና የግል ኃላፊነቶችን ያስከትላሉ፡፡
2. በኮሚሽኑ መዋቅር በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊዎች በበተሰጣቸው ሥልጣን መሰረት በማስተባበር፣ በመቆጣጠር፣ በመወሰን

stand.

24. Establishment of police complaint hearing organ of the region.

1. In accordance to this proclamation a police complaint hearing organ shall be

   Established in the commission.
2. The complaint hearing organ to be established in accordance with the provision of sub article 1 of this article shall have the following functions.
   a) It shall receive from an individual office organization or the public and investigate

      complaints. Suggestions or criticisms as regards the performance and delivery of service by the police of the Region and organs of the commission.
   b) On the basis of the complaint submitted to it. It shall order any police officer to make a reply to the complaints.
   c) It shall examine the complaint submitted to it and recommended to the commissions on measures to be taken
3. The regional police organ (member) that is ordered to reply in accordance to sub article 2 (b) of its article shall respond with 20 days.

## PART FOUR
## Miscellaneous provisions

25. Relations of the commission with the Federal police commission.

1. The commission shall have a working relation with the federal police commission concerning federal matters
2. When the federal police commission delegates power to the commission in accordance with the provision of sub article 1 of this article it shall have accountability to the federal police commission when preventing, investigation and examining the federal criminal affairs.
3. The commission shall submit to the federal police commission report and statistics on crime, traffic and security affairs for research purpose and common usage.
4. It could demand if necessary assistance, trained manpower and technical consultancy services from the federal police commission.
5. Work to ensure uniform standards on issues relating to recruitment, employment, education, training, payment of salary and allowance, Uniform wearing, dismissal, retirement age the regional police officer.

3. ኃላፊነታቸውን የመወጣት ግዴታ አለባቸው፣
4. የኮሚሽኑ አሰራር የተጠያቂነትና የግልጽነት መርህን የተከተለ መሆን ይኖርበታል፣
5. የኮሚሽኑ አሰራር የህዝብን ተሳትፎ መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፣
6. የኮሚሽነሩ አሠራር የፍትሀዊነትና የገለልተኝነት የአሰራር መርህን የተከተለ ይሆናል፡፡

## 27. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ/ 6 /የተመለከቱትን ከወንጀል መከላከልና ምርመራ ጋር የተያያዙ ተግባራትን ሲያከናውን የሚመለከታቸው ሁሉ የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## 28. <u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች</u>

1. የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን አዋጅ ቁጥር 39/1995 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፣
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ህግ፣ደንብ እና መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 29. <u>የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

የክልሉ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኮሚሽኑ ተላልፈዋል፡፡

## 30. <u>ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>

የክልሉ መስተዳደር ም/ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈለጉትን ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 31. <u>መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

ኮሚሽኑ የዚህን አዋጅ ተከትሎ የሚወጣውን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 32. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከጸደቀበት ---- ቀን /2007 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አህመድ ናስር
የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልላዊ መንግስት ፕሬዘዳንት
ቀን የካቲት 02/ 2007 ዓ.ም
አሶሳ

## 26. <u>Working principle</u>

1. Teamwork shall be maintain governing rule in practical exception of activates by heads and employs found at all levels within.
2. Heads found at all levels within the police structure in the Region are under an obligation to exercise the power entrusted to them in accordance with their allocate function.
3. The heads and employees of the police in the region shall carry out function in a coordinated team beginning from the formulation of work plan up to execution and evaluation.
4. The activities of the police shall be based on the participation of the public.
5. The activities of the police shall be based on fairness and impartiality.

## 27. <u>Obligation to cooperate</u>

Every concerned person shall have the obligation to cooperate with the commission in discharging its duties relating to crime prevention and investigation as provided for article 6 of this proclamation.

## 28. <u>Repelled and inapplicable laws</u>

1. The regional police commission proclamation No.39/2003 shall be repealed.
2. Any law, regulation and directive or customary practice inconsistent with this proclamation shall not be applicable to matters specified in this proclamation.

## 29. <u>Transfer of Rights and Duties</u>

The rights and duties of the Regional police hereby transferred to the commission.

## 30. <u>Power to Issus Regulation</u>

The Administration council of the Region shall have the power to issue regulations necessary to implement this proclamation.

## 31. <u>Power to issue Directive</u>

The commission shall have the power to issue directive necessary to implement this proclamation

## 32. <u>Effective Date</u>

It shall be effective upon publication in the Region's lissane Hig.

Ahimed Nasire
President of the Benshangul Gumuze Regional state
Fab 10/ 2015 G.c.
Assosa